የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

# የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔ ናሙና (Template)

1. መደበኛ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ እና
2. አስቸኳይ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

አዲስ አበባ
ሕዳር 2018 ዓ.ም

**__________.አ.ማ.**

**የባለአክሲዮኖች_____ኛ________ጠቅላላ ጉባዔ**

***ቃለ ጉባዔ ቁጥር______***

1. **ጠቅላላ ጉባዔ የተደረገበት ቀን፣ሰዓትና ቦታ**
   - ሀ. ቀን፡-____________________
   - ለ. ሰዓት-፡____________________
   - ሐ. ቦታ፡-____________________

2. **የጉባዔው ጥሪ አደራረግ**

   ይህ የባለአክሲዮኖች_____ኛ________ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በንግድ ሕግ ፣አንቀጽ 366(___)፣ አንቀጽ 367(___)፣ አንቀጽ_____እና አንቀጽ 370[1] መሠረት ከጉባዔው ዕለት 24 ቀናት አስቀድሞ *(አገር-አቀፍ/ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን ባስመዘገበው አድራሻ በተላከ ደብዳቤ ወይም ለዚሁ ዓላማ ለማህበሩ በሰጠው ኢሜይል ወይም ሌላ አስተማማኝ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ)*[2] አማካኝነት እንዲሁም በማህበሩ ድረ-ገጽ *(የድርጅቱ ድረ-ገጽ አድራሻ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሆነ፡ https://nbe.gov.et/ ተብሎ መጻፍ አለበት)* በመለጠፍ በማህበሩ *(በዳይሬክተሮች ቦርድ፣ኦዲተሮች፣ሒሳብ አጣሪዎች፣ፍርድ ቤት፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወዘተ…)*[3] ተጠርቷል፡፡

3. **የጉባዔው ሰብሳቢ፣ድምጽ ቆጣሪዎች፣ጸሐፊ፣በጉባዔው የተገኙ ዳይሬክተሮች እና ታዛቢዎች**

   3.1 **የጉባዔው ሰብሳቢ**

   የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በጉባዔው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢው ካልተገኘ ምክትል ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢ ካልተገኘ ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል በሹመት ቀደምትነት ያለው፣በሹመት ቀደምትነት ያለው ዳይሬክተር ካልተገኘ በጉባዔው የተመረጠው ዳይሬክተር ወይም ጉባዔው የተጠራው ከማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውጭ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል ከሆነ ይህ ጉባዔውን የጠራው አካል ወይም ተወካዩ የጉባዔው ሰብሳቢ ሆኖ ስለመምራቱ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 379 መሠረት በቃለ-ጉባዔው በግልጽ መስፈር አለበት፡፡

---

1 በንግድ ሕግ አንቀጽ 390 መሠረት ይህንኑ ስለባለአክሲዮኖች ጉባዔ አጠራር የተመለከተውን የተለመደው ሥርዓት ሳይከተሉ ሁሉም የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በስምምነት ጉባዔ በማካሄድ በሕግ አግባብ በጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣን ስር በሚወድቅ ማንኛውም ጉዳይ ላይ መወያየት እና ውሳኔ ማሳለፍ ይቻላል፡፡ ሆኖም ጉባዔው በዚህ አግባብ ስለመደረጉ በግልጽ በቃለ-ጉባዔው መገለጽ/መጻፍ አለበት፡፡

2 ከእነዚህ በቅንፍ የተቀመጡ የጉባዔ ጥሪ ማድረጊያ ዘዴዎች ማህበሩ ጉባዔው ለመጥራት የተጠቀመው ዘዴ በግልጽ መጠቀስ አለበት፤ እንዲሁም የጉባዔው ጥሪ በማናቸውም ዘዴ ቢደረግም የጉባዔው ጥሪ የተደረገበት ሰነድ ግልባጭ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 387(3ረ) መሠረት ከቃለ-ጉባዔው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤ካልሆነ ግን በቃለ-ጉባዔው ላይ ምንም ዓይነት ዝርዝር አስተያየት ወይም ማብራርያ ሳይሰጥ በመጣበት አግባብ ለአክሲዮን ማህበሩ ተመላሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡ በተጨማሪ ለማሳያ የሚሆን የጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ ከዚህ የቃለ-ጉባዔ ናሙና ጋር ተያይዟል፡፡

3 ከእነዚህ በቅንፍ የተዘረዘሩ አካላት መካከል በትክክል ጉባዔውን የጠራው አካል ተለይቶ በቃለ-ጉባዔው መገለጽ አለበት፡፡

### 3.2 <u>የጉባዔው ድምጽ ቆጣሪዎች እና የጉባዔው ጸሐፊ</u>

ጉባዔውን ለመጀመር በንግድ ሕጉ አንቀጽ 380(1) መሠረት በጉባዔው በባለአክሲዮንነት ወይም በወኪልነት ከተገኙ እና ፈቃደኛ ከሆኑት_______ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ባላቸው ባለአክሲኖች መካከል በተደረገ ስምምነት ከዚህ በታች በተቀመጠው ሠንጠረዥ ስማቸው የተዘረዘረው______ባለአክሲዮኖች የጉባዔው ድምጽ ቆጣሪዎች ሆነው ተመርጠዋል[4]:: እንዲሁም የማህበሩ ቋሚ ጸሐፊ የጉባዔው ጸሐፊ ሆኖ ተሰይሟል[5]::

| ተ.ቁ | ስም | ኃላፊነት | በተወካይ ከሆነ የተወካይ ስም |
|---|---|---|---|
| 1. | | ድምጽ ቆጣሪ | |
| 2. | | ድምጽ ቆጣሪ | |
| 3. | | የጉባዔው ጸሐፊ | |

### 3.3 <u>በጉባዔው የተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት</u>

| ተ.ቁ | ስም | ተወካይ | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1. | | | ሰብሳቢ[6] |
| 2. | | | ም/ሰብሳቢ[7] |
| 3. | | | አባል |

### 3.4 <u>በጉባዔው ያልተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት</u>[8]

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | | |
| 2. | | |

### 3.5 <u>በጉባዔው የተገኙ ታዛቢዎች</u>[9]

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | የወከላቸው ተቋም |
|---|---|---|
| 1. | | |

## 4. <u>ምልዓተ ጉባዔ</u>

---

4 ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ድምጽ ለመቁጠር ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም በጉባዔ የተገኙት ባለአክሲዮኖች ሌላ ሰው መምረጥ ከፈለጉ ጉባዔው እንደተጀመረ የድምጽ ቆጠራውን ለማድረግ የሚያስፈልጉ ድምጽ ቆጣሪዎች በንግድ ሕግ አንቀጽ 380(2) መሰረት ጉባዔው የተወሰኑ ባለአክሲዮኖችን መምረጥ ይችላል፡፡

5 የማህበሩ ጸሐፊ የቋሚ ቅጥር ደብዳቤ ግልባጭ ሁልጊዜ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚቀርበው ቃለ-ጉባዔ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤ካልሆነ ግን በቃለ-ጉባዔው ላይ ምንም ዓይነት ዝርዝር አስተያየት ወይም ማብራሪያ ሳይሰጥ በመጣበት አግባብ ለአክሲዮን ማህበሩ ተመላሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡

6 የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፤ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ም/ሰብሳቢ፤ ም/ሰብሳቢ በማይኖርበት ደግሞ በንግድ ሕግ አንቀጽ 379 መሠረት የሚሰየም ሰው የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

7 እንደአስፈላጊነቱ በንግድ ሕግ አንቀጽ 300(2) መሠረት በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ወይም በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስምምነት የሚመረጥ አባል ነው፡፡

8 በጉባዔ ያልተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከሌሉ(ሁሉም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በጉባዔው ከተገኙ) ከዚህ የቃለ-ጉባዔው ንዑስ-ርዕስ ቀጥሎ/ፊትለፊት ***"የለም"*** በማለት በአጭሩ ይገለጽ፤እንዲሁም ከስር የተቀመጠው ሠንጠረዥ መሠረዝ አለበት፡፡

9 በጉባዔው የተገኙ ታዛቢዎች ካልነበሩ ከዚህ የቃለ-ጉባዔው ንዑስ-ርዕስ ቀጥሎ/ፊትለፊት ***"የለም"*** በማለት በአጭሩ ይገለጽ፤እንዲሁም ከስር የተቀመጠው ሠንጠረዥ መሠረዝ አለበት፡፡

4.1 ጠቅላላ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ብዛት=____________________

4.2 ጠቅላላ የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ[10] የአክሲዮን ብዛት=____________________

4.3 በጉባዔው የተገኙት የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ብዛት_____ሲሆኑ የያዙት የአክሲዮን ብዛትም____________(______%) ነው፡፡

4.4 በጉባዔው ያልተገኙ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ብዛት_____ሲሆኑ የያዙት የአክሲዮን ብዛት____________(______%) ነው፡፡

4.5 ጉባዔውን ለመጀመር አስፈላጊ የሆነ አነስተኛ የአክሲዮን ብዛት____________ወይም (______%) ነው፡፡

በዚሁ መሠረት በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ_____እና በንግድ ሕጉ አንቀጽ_____(_____)[11] መሠረት ከጠቅላላ የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) _____% የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ስለተገኙ በጉባዔው አጀንዳዎች ላይ ተወያይተው ውሳኔ ለማሳለፍ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ በድምጽ ቆጣሪዎች ተረጋግጦ ጉባዔው ቀጥሏል፡፡ በጉባዔው የተገኙትን ወይም ወኪል የላኩትን ባለአክሲዮኖች ስምና አድራሻቸው፣ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያለውን የአክሲዮን መጠንና የሚሰጠው የድምፅ ቁጥር የሚያሳይ የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ጋር አባሪ ሆኖ ተያይዞ ቀርቧል፡፡

## 5. የጉባዔ አጀንዳዎች[12]

5.1 የጉባዔው አጀንዳዎች ማጽደቅ[13]

5.2 ……………..

5.3 ……………..

5.4 ……………..

5.5 ሌሎች ጉዳዮች[14]……

---

[10] ጠቅላላ የማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ጉባዔው በሚደረግበት ጊዜ በሙሉ የተከፈለ ከሆነ ***"የተፈረመ እና የተከፈለ"*** ተብሎ መጻፍ አለበት፡፡

[11] እንደጉባዔው ዓይነት (መደበኛ ወይም አስቸኳይ ሊሆን ይችላል) የንግድ ሕግ አንቀጽ 398 ወይም አንቀጽ 402 አግባብነት እና ተቀባይነት ካለው/ካላቸው ንዑስ-አንቀጽ/ጾች ጋር መጠቀስ አለበት፡፡

[12] ምን ዓይነት ጉባዔ በምን ዓይነት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ የማሳለፍ ስልጣን እንዳለው የሚያሳይ አጭር ማብራሪያ (Brief Illustrative Note) ከዚህ የቃለ-ጉባዔ ናሙና ጋር ተያይዟል፡፡ በተጨማሪ እያንዳንዱ አጀንዳ በዚህ ንዑስ-ርዕስ ሲጻፍ ይሁን ከዚህ በታች በንዑስ-ርዕስ 6 የጉባዔው ውይይት አጭር ማጠቃለያ፣ የተሠጡትን ድምጾችና ውሳኔዎች ለማሳየት በድጋሚ በቅድም ተከተል በሚጻፍበት ጊዜ ምንም ዓይነት ቀላል ማሻሻያም ቢሆን ሳይደረግበት በጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ በተገለጸበት አግባብ በድጋሚ መጻፍ አለበት፡፡

[13] በጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ ላይ ይህ አጀንዳ ከመጀመሪያው ቢካተትም ባይካተትም በጉባዔው ውይይት የሚደረግባቸው አጀንዳዎች በባለአክሲዮኖች የጸደቁ ስለመሆናቸው በቃለጉባዔው በግለጽ መታየት አለበት፡፡ይሄውም ጉባዔው መጀመሪያ በጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ በተገለጹ አጀንዳዎች ብቻ ነው ወይይቶች አድርጎ ውሳኔዎች ያስተላለፈው ወይስ ጉባዔው በንግድ ሕግ አንቀጽ 305(1)፣ አንቀጽ 372(2 እና 3)፣ አንቀጽ 328፣አንቀጽ 346፣ አንቀጽ 387(2) እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች በሚፈቅዱት መሠረት በተጨመሩ አጀንዳዎች ጭምር ውይይት በማድረግ ነው ውሳኔዎች ያስተላለፈ የሚለው ጉዳይ ቃለጉባዔ በራሱ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መረጃ መያዝ አለበት፡፡

[14] በዚህ ስር ሊጨመሩ የሚችሉት አጀንዳዎች በጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ ባይነገሩም ጠቅላላ ጉባዔው በጉባዔው ቀን በአጀንዳ ይዞ ተወያይቶ ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ለምሳሌ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 305 እና አንቀጽ 346 ቅደምተከተል መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የውጭ ኦዲተሮች ሹመት ስለመሻር እና በሌሎች ስለመተካት፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከሥራ ኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ ላጠፉት ጥፋት በንግድ ሕግ

5.6 የጉባዔውን ቃለጉባዔ ስለማጽደቅ[15]

## 6. የጉባዔው ውይይት አጭር ማጠቃለያ፣ የተሠጡትን ድምጾችና ውሳኔዎች

**6.1** አጀንዳ 5.1፡......................................

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

ለ. የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና ጉባዔው ያሳለፈውን ውሳኔ

**6.2** አጀንዳ 5.2፡......................................

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

ለ. የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና ጉባዔው ያሳለፈውን ውሳኔ

**6.3** አጀንዳ 5.3፡......................................

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

ለ. የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና ጉባዔው ያሳለፈውን ውሳኔ

## 7. ለጉባዔው የቀረቡ ሰነዶች[16]

በዚህ የቃለ-ጉባዔው ንዑስ-ርዕስ ስር የሚዘረዘሩ ለጉባዔው የቀረቡ ሰነዶች እንደጉባዔው ዓይነት ***(ለምሳሌ ጉባዔው አስቸኳይ ወይም ዓመታዊ ወይም ዓመታዊ ያልሆነ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሊሆን ይችላል)*** ሊለያዩ እንደሚችሉ የሚታወቅ ቢሆንም እንደሁኔታው የሚከተሉት ሰነዶች በዚህ ዝርዝር ስር ሊካተቱ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

**7.1** እ.ኤ.አ የ202__/__ የሒሳብ ዓመት በዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበ______ ገጽ ሪፖርት፡፡

**7.2** እ.ኤ.አ የ202__/__ የሒሳብ ዓመት በዳይሬክተሮች ቦርድ በቀረበው የሪፖርት ላይ ተገቢው ውይይት ተደርጎበት፤ ነገር ግን ጉባዔው በአጀንዳው ላይ ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት ጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርቱ እንዲያጸድቀው ወይም ውድቅ እንዲያደርገው የውጭ ኦዲተሩ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 349(2) መሠረት ጉባዔው በተደረገበት ቀን በጉባዔው ተገኝቶ በጽሑፍ ያቀረበው አጭር የውሳኔ ሀሳብ______ ገጽ፡፡

**7.3** እ.ኤ.አ የ202__/__ የሒሳብ ዓመት በዳይሬክተሮች ቦርድ በቀረበው የትርፍ ክፍፍል አጀንዳ ላይ ተገቢው ውይይት ተደርጎበት፤ ነገር ግን ጉባዔው በአጀንዳው ላይ ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት የውጭ ኦዲተሩ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 349(2) መሠረት ጉባዔው በተደረገበት ቀን በጉባዔው ተገኝቶ የሰጠው አጭር አስተያየት______ ገጽ፡፡

---

አንቀጽ 328 መሰረት ክስ እንዲመሰረትባቸው ወይም የተጀመረው ክስ ለመተው ወይም በግልግል ለመጨረስ ውሳኔ ለመስጠት፣ ጉባዔው ሥራ ከመጀመሩ በፊት በስብሰባው ላይ ከተገኙት ባለአክሲዮኖች መካከል በጉባዔው ላይ የተደረገው ውይይት እና የተላለፈው ውሳኔ በትክክል በቃለ-ጉባዔ ስለመስፈሩ አረጋግጠው በዳይሬክተሮች ቦርድ እና በማህበሩ ጸሐፊ ምትክ የሚፈርሙ ባለአክሲዮኖች በንግድ ሕግ አንቀጽ 387(2) መሰረት መምረጥን ወዘተ...የሚመለከቱ እና ሌሎች በሕግ አግባብ የተፈቀዱ ጉዳዮች ካልሆኑ በስተቀር ሌሎች በጉባዔው ቀን የሚጨመሩ አጀንዳዎችም ሆነ በአጀንዳዎች ላይ የሚተላለፉ ውሳኔዎች ሕጋዊ ተቀባይነት እንደማይኖራቸው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

[15] በጉባዔው ውይይት ተደርጎባቸው የተወሰኑ ውሳኔዎች ባለአክሲዮኖች በተስማሙበት አግባብ በቃለጉባዔው የተመዘገቡ ስለመሆናቸው በድምጽ ማረጋገጫ እንዲሰጡበት ቢደረግ በኃላ ውሳኔዎቹን ባለመቀበል ውድቅ እንዲደረጉ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ለመቀነስ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

[16] በንግድ ሕግ አንቀጽ 387(3/ሬ) መሠረት ለጉባዔው የቀረቡትን ሰነዶች ዝርዝር በመግለጽ ከቃለ-ጉባዔው ጋር አባሪ አድርጎ ማያያዝ እና ስለመያያዛቸው በቃለ-ጉባዔው መገለጽ አለበት፡፡

7.4 እ.ኤ.አ የ202__/__ የሒሳብ ዓመት በውጭ ኦዲተር የቀረበ_______ ገጽ ሪፖርት፡፡

7.5 እንደነገሩ ሁኔታ በነባር እና አዳዲስ ባለአክሲዮኖች የተገዙ አክሲዮኖች እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውር የሚያሳዩ ዝርዝር ሠንጠረዥ_______ ገጽ፡፡

7.6 የአክሲዮን ማህበሩን የካፒታል ዕድገት ለማሻሻል የዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ/ልዩ ሪፖርት _______ ገጽ፡፡

7.7 ረቂቅ የአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ_______ ገጽ፡፡

7.8 ……………………………………..

በተጨማሪ ጉባዔው ጥሪ የተደረገበት ዘዴ እና ይዘት የሚያሳይ **የጉባዔው የጥሪ ማስታወቂያ** እና **የአክሲዮን ማህበሩ ጸሐፊ የቅጥር ደብዳቤ** ግልባጭ/ኮፒ በንግድ ሕግ አንቀጽ 3873/ረ) መሠረት ለጠቅላላ ጉባዔ የሚቀርቡ ሰነዶች ባይሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለቁጥጥርና ለክትትል ስለሚፈልጋቸው የግድ ከቃለ-ጉባዔው ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ በአጽንኦት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 8. የአክሲዮን ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ጸሐፊ ማረጋገጫ[17]

እኛ የ__________________አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ጸሐፊ ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ሰነድ ጋር አባሪ ሆኖ የተያያዘው የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ላይ በየስማቸው የፈረሟቸው እና የከፈሏቸው አክሲዮኖች ብዛት በስማቸው አንጻር በተመለከቱት ትይዩ የፈረሙ ባለአክሲዮኖች ወይም ተወካዮቻቸው ______________ቀን 201_____ዓ.ም በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ______ኛ_______ጠቅላላ ጉባዔ ላይ መገኘታቸውንና ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው በዚህ ቃለ-ጉባዔ ሰነድ ላይ የተገለጹትን ውሳኔዎች ማሳለፋቸው በንግድ ሕግ አንቀጽ 387(1) መሠረት በሙሉ ስምና ፊርማችን እያረጋገጥን፣ በሰነዶቹ ላይ ስለተገለጹት ጉዳዮች እና ስለተላለፉ ውሳኔዎች ትክክለኛነት ስማቸው በሰነዶቹ ላይ በተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ለሚነሳ ማናቸውም የመብት ጥያቄ ኃላፊዎች መሆናችንን ጭምር እናረጋግጣለን፡፡

| ተ.ቁ | የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የጉባዔ ጸሐፊ ስም ዝርዝር | ኃላፊነት | ፊርማ (በተወካይ ከሆነ የተገኘው የተወካይ ስም ይጻፍ) |
|---|---|---|---|
| 1. | | ሰብሳቢ | |
| 2. | | ም/ሰብሳቢ | |
| 3. | | አባል | |
| 4. | | የጉባዔ ጸሐፊ[18] | |

[17] በዚህ የቃለ-ጉባዔው ንዑስ-ርዕስ ስር የተገለጸው አንዱ ማረጋገጫውን የመስጠት አማራጭ በሕግ እና በተግባር የተለመደ ቢሆንም የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔው ሥራ ከመጀመሩ በፊት አስቀድሞ በጉባዔው የጥሪ ማስታወቂያ በአጀንዳ መልክ ባይነገርም ስብሰባው ላይ ከተገኙት ባለአክሲዮኖች መካከል በጉባዔው ላይ የተደረገው ውይይት እና የተላለፈው ውሳኔ በትክክል በቃለ-ጉባዔ መስፈሩን አረጋግጠው በዳይሬክተሮች ቦርድ እና በማህበሩ ጸሐፊ ምትክ የሚፈርሙ ሦስት ባለአክሲዮኖች በንግድ ሕጉ አንቀጽ 387(2) መሠረት በአማራጭ መመረጥ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

[18] የማህበሩ ጸሐፊ በዋና ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በቦርዱ የሚጸድቅ ተቀጣሪ ሲሆን ተጠሪነቱም በንግድ ሕግ አንቀጽ 340 መሰረት ለዋና ስራ አስኪያጅ ነው፡፡

## __________.አ.ማ.

## የባለአክሲዮኖች_____ኛ________ጠቅላላ ጉባዔ

## የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ[19]

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | አድራሻ[20] | | | | ያለውን የአክሲዮን መጠን | | የሚሰጠውን የድምጽ ቁጥር[21] | ፊርማ | ባለአክሲዮኑ ለጉባዔው ተወካይ ከላከ የተወካዩ ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ከተማ | ቀበሌ | የቤ/ቁጥር | የተፈረመ | የተከፈለ | | | |
| 1. | | | | | | | | | | |
| 2. | | | | | | | | | | |

**የጉባዔው ጸሐፊ ማረጋገጫ**

እኔ የ______________________________የጉባዔው ጸሐፊ ከቃለ-ጉባዔው ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው ይህ የጉባዔ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ላይ________________ቀን 201___ዓ.ም በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ_______ኛ___________ጠቅላላ ጉባዔ በጉባዔው የተገኙትን ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች በየስማቸው ትይዩ የተጻፈው ስምና አድራሻቸው፣ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያለውን የአክሲዮን መጠንና የሚሰጠው የድምፅ ቁጥር በትክክል የተገለጸ ስለመሆኑ አረጋግጠው የፈረሙበት ስለመሆኑ በንግድ ሕግ አንቀጽ 378(2) መሠረት በስሜና በፊርማዬ–አረጋግጣለሁ።

ሙሉ ስም:_____________________________

ፊርማ:________________

ቀን:________________

---

[19] መደበኛ እና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች በአንድ ቀን ተከታትለው ቢደረጉም ለእያንዳንዱ ጉባዔ የራሱ የሆነ የጉባዔ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ሊዘጋጅለት ይገባል።

[20] በዚህ የባለአክሲዮኖች አድራሻ ሥር ሊካተቱ የሚችሉ የባለአክሲዮኖች ዝርዝር መረጃዎች በአክሲዮን ማህበሩ ምርጫ ለዚህ ዓላማ ብቻ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም አክሲዮን ማህበሩ መካተት አለባቸው ብሎ የወሰናቸው የባለአክሲዮኖች ዝርዝር አድራሻ የሚገልጹ የሁሉም ባለአክሲዮኖች መረጃዎች ግን በአግባቡ እና ወጥነት ባለው መልኩ ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፤ ምንም ዓይነት ያልተሟላ መረጃ ሊኖር አይገባም።

[21] በመርህ ደረጃ ባለአክሲዮኖች በጉባዔው የሚሰጡት ድምጽ ካላቸው የተፈረመ የአክሲዮን ድርሻ እኩል ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድ ቢሆንም፤ ይህንኑ ግምት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 271፣275(2)፣289(7)፣375፣384፣ እና 451(2) እንዲሁም በተለይ በባንክ እና በኢንሹራንስ ድርጅቶች ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን የሆኑት ሰዎች በጠቅላላ ጉባዔዎች የሚሰጡት ድምጽ በመመሪያ ቁጥር SBB/89/2024 አንቀጽ 10.1 እና በመመሪያ ቁጥር 105/2020 (SIB/32/2012) አንቀጽ 6.1 መሠረት ሊገደብ ወይም ለውሳኔ በቀረበው አጀንዳ መሠረት ሊለያይ ስለሚችል እያንዳንዱ በጉባዔው የተገኘው ባለአክሲዮን የሚሰጠው የድምጽ ቁጥር በዚህ የሠንጠረዡ አምድ(Column) ተሟልቶ ካልቀረበ የጉባዔው ውሳኔዎች ውጤት አልባ እንዲሆኑ በማድረግ ጉባዔው እስከ ማስደገም የሚደርስ አላስፈላጊ ውጤት እንዳያስከትል መረጃው በከፍተኛ ጥንቃቄ እና በትክክል ተሟልቶ መቅረብ አለበት።

## **ማሳሰቢያ**

**ከዚህ በላይ በተገለጸው አግባብ እንዲዘጋጅ የታሰበው የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የቃለ-ጉባዔ ናሙና የተለያዩ ክፍሎች ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ታስበው በግርጌ ማስታወሻ *(foot notes)* የተጻፉ ማብራሪያዎች ከቃለ-ጉባዔው የመጨረሻ ረቂቅ ሰነድ ተሰርዘው ንጹህ የሆነ ሰነድ ብቻ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንደሚቀርብ በጥብቅ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡**

የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔ
ናሙና

## ዓመታዊ[22] የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ

ዓመታዊ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በየዓመቱ እያንዳንዱ የሒሳብ ዓመት ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ ባሉት አራት ወራት ውስጥ አንድ ጊዜ የሚደረግ ነው፡፡ ሆኖም የጊዜ ገደቡ በመመስረቻ ጽሑፍ በመደንገግ እስከ ስድስት ወር ሊራዘም ይችላል፡፡

### ምልዓተ ጉባዔ

ሀ. በንግድ ሕግ አንቀጽ 398(1) መሠረት በመጀመርያው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ (ካፒታል) አንድ አራተኛ (25%) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች በጉባዔው መሳተፍ አለባቸው፡፡

ለ. በንግድ ሕግ አንቀጽ 398(3) መሠረት በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ግምት ውስጥ ሳይገባ በተገኙት አክሲዮኖች ጉባዔውን ማካሄድና ውሳኔዎች ማሳለፍ ይቻላል፡፡

### ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልግ ድምፅ

በንግድ ሕግ አንቀጽ 398(4) መሠረት የጉባዔው ውሳኔዎች የሚተላለፉት በጉባዔው በተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች አብዛኛውን ካፒታል በሚወክሉት ድምጽ (**Simple Majority**) ከተደገፉ ነው፡፡

### የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣን

❖ በንግድ ሕግ አንቀጽ 394 መሠረት የማህበሩ የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ፣ የትርፍና ኪሳራ ሒሳብ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት፣ የኦዲተሮችን ሪፖርት ካለም የተቆጣጣሪ ቦርድን ሪፖርት፣ አዳምጦ ***የማሻሻል*** ወይም ***የማጽደቅ***፣ ወይም ***ያለመቀበል***፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ***በትርፍ አመዳደብና አከፋፈል*** እንዲሁም በአጠቃላይ ያለፈውን የሒሳብ ዓመት ማጠቃለያ የተመለከቱ የሒሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የማሳለፍ፤ እዚህ ላይ ***በተለይ ከዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጋር በተያያዘ፡-***

☛ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 314 መሠረት ለዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በቀረበው ወይም በሚቀርበው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት/መግለጫ ለእያንዳንዱ የአክሲዮን ማህበሩ የቦርድ አባል እና ዋና ሥራ አስኪያጅ/አስፈጻሚ የተከፈለውን አጠቃላይ ***የድካም ዋጋ፣በየጊዜው የሚከፈለውን መጠን እና ሌሎች በዓይነት የተሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች*** (ለምሳሌ የቤት አበል፣ መኪና...) እንዲሁም ***የተሰጠ ብድር ወይም የተገባ ዋስትና*** ካለ በሪፖርቱ ውስጥ በዝርዝር እንዲሁም በቃለ-ጉባዔው ላይ በጥቅሉ መገለጽ አለበት፤ከሌለም በእያንዳንዱ የክፍያ ወይም የጥቅማ ጥቅም ምድብ የለም ተብሎ መገለጽ አለበት፡፡

[22]አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማንኛውም አክሲዮን ማህበር በንግድ ሕግ አንቀጽ 393(3) መሠረት ተጨማሪ ዓመታዊ ያልሆኑ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች ሊያደርግ ይችላል፡፡

- ለዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በቀረበው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የአክሲዮን ማህበሩ የውጭ ኦዲተር በንግድ ሕግ አንቀጽ 349(2) መሠረት ራሱ ከሚያቀርበው ሪፖርት ውጭ ጉባዔው በአጀንዳው ላይ ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት ጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርቱ እንዲያጸድቀው ወይም ውድቅ እንዲያደርገው ጉባዔው በተደረገበት ቀን በጉባዔው ተገኝቶ በጽሑፍ አጭር የውሳኔ ሀሳብ ሳይሰጥበት ውሳኔ መወሰን ወይም ይህንኑ የሕግ ድንጋጌ ለመከተል በማሰብ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት እና የውጭ ኦዲተሩ ሪፖርት ለየብቻቸው ከቀረቡ በኋላ በአንድ ላይ ውይይት ተደርጎባቸው ማጸደቅ፤እና
- የአክሲዮን ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ራሱን ችሎ በሚያቀርበው የትርፍ ክፍፍል አጀንዳ ስር ተገቢውን ውይይት አድርጎ፤ ነገር ግን ጉባዔው በአጀንዳው ላይ ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት የውጭ ኦዲተሩ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 349(2) መሠረት ጉባዔው በተደረገበት ቀን በጉባዔው በአካል ተገኝቶ በውሳኔ ሀሳቡ ላይ ሙያዊ አስተያየት ሳይሰጥበት ማስወሰን፤

በተጋጋሚ የሚያጋጥሙ ቀላል በሚመስሉ የሕግ ጥሰቶች ምክንያት የአጀንዳው ውሳኔ ሙሉበሙሉ ሕጋዊ ተቀባይነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ስለሚችል የሚመለከታቸው የአክሲዮን ማህበሩ የአመራር አካላት በተለይም የዳይሬክተሮች ቦርድ ከዚህ ጊዜ በኋላ ለዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በሚያቀርቡት ሪፖርት ይዘት ላይ እና ከላይ በተጠቀሱ ሁለት አጀንዳዎች ውሳኔ ሲሰጥ መፈጸም ባለባቸው የሕግ ስነ-ስርዓት ቅደም ተከተል አፈጻጸም ላይ በከፍተኛ ጥንቃቄ ኃላፊነታቸው እንዲወጡ ይጠበቃል፡፡

- ❖ እንደአስፈላጊነቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላትን ወይም ኦዲተሮችን የመሾም ወይም የመሻር እንዲሁም የሥራ ዋጋቸውን የመወሰን፤
- ❖ የአክሲዮን ዝውውር የማጽደቅ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘም፡-
- አክሲዮኖች ከማህበሩ ገዝተው የገቡና ከነባር ባለአክሲዮኖች አክሲዮን በተለያዩ መንገዶች ተላልፎላቸው የገቡ ሰዎች ባለአክሲዮንነታቸው በየዓመቱ መጨረሻ በዚህ ጉባዔ ይጸድቅላቸዋል፡፡
- እነዚህ የአክሲዮን ዝውውሩ የፀደቀላቸው ሰዎች በዕለቱ በሚደረገው ጉባዔ ከድምጽ መስጠት፣ በዳይሬክተርነት ከመመረጥና[23] ከመሳሰሉት ከባለአክሲዮንነት የሚመነጩ መብቶች ሁሉ የሚጠበቅላቸው ይሆናል፡፡ ሆኖም በእነዚህ መብቶች ለመጠቀም ዝውውሩ አስፈላጊ ***ሕጋዊ ቅድመ ሁኔታዎችን*** አሟልቶ በአክሲዮን ማህበሩ የባለአክሲዮኖች መዝገብ ወይም አግባብነት ያለው ሕግ በሚጠይቀው መንገድ ***በማዕከላዊ የሰነድ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት*** ላይ አስቀድሞ ከተመዘገበ ብቻ ይሆናል፡፡
- ❖ በጠቅላላ በሕግ አግባብ ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በግልጽ ተለይተው ከተሰጡት ጉዳዮች በስተቀር በሌሎች የማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሚወስንባቸው ጉዳዮች ላይ ሁሉ መደበኛ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡

## የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ

[23] አክሲዮን ማህበሩ በባንክ አገልግሎት የንግድ ሥራ የተሰማራ ከሆነ የአክሲዮን ዝውውሩ የፀደቀላቸው አዳዲስ ባለአክሲዮኖች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ለመመረጥ ያላቸው መብት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 20.4 ላይ የተቀመጠው ገደብ ታሳቢ በማድረግ መፈጸም አለበት፡፡

የአክሲዮን ማህበር አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ **በሕግ ተለይተው በተገለጹ ጉዳዮች ብቻ ውሳኔ ለማሳለፍ በማናቸውም ጊዜ ጉባዔውን ለመጥራት በሕግ ስልጣን በተሰጣቸው አካላት የሚጠራ እና በባለአክሲዮኖች የሚካሄድ ጠቅላላ ጉባዔ ነው**፡፡

**ምልዓተ ጉባዔ**

- በንግድ ሕግ አንቀጽ 402(2 እና 3) *መሠረት* የማህበሩን ዜግነት ለመለወጥ ወይም አንድ ባለአክሲዮን ከፈቃዱ ውጪ በማህበሩ ውስጥ ተጨማሪ መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈስ ውሳኔ ለማሳለፍ ጉባዔው ከተጠራ የግድ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው ባለአክሲዮኖች በሙሉ በጉባዔው መገኘት አለባቸው፡፡
- ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ውጭ ውሳኔ ለማሳለፍ የሚሰበሰብ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በንግድ ሕግ አንቀጽ 402(4) *መሠረት* ምልዓተ ጉባዔ ተሟልቷል የሚባለው፡-
  - ሀ. በመጀመሪያው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ ሦስተኛ (33.34%) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በጉባዔው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡
  - ለ. በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ አራተኛ (25%) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በጉባዔው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡
  - ሐ. በሦስተኛ ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ግምት ውስጥ ሳይገባ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡

**ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልግ ድምፅ**

- በንግድ ሕግ አንቀጽ 402(2 እና 3) ስር በተጠቀሱ ጉዳዮች ውሳኔ የሚተላለፈው በሙሉ ድምጽ ድጋፍ (**Unanimous Vote**) ነው፡፡
- በሌሎች የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች ውሳኔዎች የሚተላለፉ በንግድ ሕግ አንቀጽ 402(1) *መሠረት* በጉባዔ በተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች ከወከሉት ካፒታል ሁለት ሦስተኛውን (66.67%) በሚወክሉት የባለአክሲዮኖች ድምጽ (**Qualified Majority**) ከተደገፈ ነው፡፡

**የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣን**

በንግድ ሕግ አንቀጽ 400 እንደተደነገገው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

***ሀ. የማህበሩን መመስርቻ ጽሑፍ የማሻሻል፤***

የሚሻሻለው የመመስረቻ ጽሑፍ ሙሉውን ይዘት ካልሆነ በአጀንዳው የውሳኔ ክፍል ከዚህ በፊት የነበረው የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ_______ከዚህ በታች በተገለጸው የተሻሻለው አዲስ አንቀጽ _______ ተተክቷል ተብሎ እያንዳንዱ የተሻሻለው ***(ንዑስ)-አንቀጽ*** በትዕምርተ-ጥቅስ (**Quotation Mark**) ውስጥ በማስቀመጥ ተቀርጾ መቅረብ አለበት፡፡

**ለ. የማህበሩን ዋና ገንዘብ የማሳደግ ወይም የመቀነስ፤**

- በማንኛውም ጊዜ **<u>በጥሬ ገንዘብ</u>** ወይም **<u>የዕዳ ሰነዶችን ወደ አክሲዮን በመለወጥ</u>** የሚከፈሉ አዳዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት የሚደረገው የአክሲዮን ማህበሩ የካፒታል ዕድገት ውሳኔ ፈራሽ እንዳይሆን በፊት ተፈርመው ያልተከፈሉ አክሲዮኖች በሙሉ መከፈል አለባቸው ወይም በፊት ተፈርመው ያልተከፈሉ አክሲዮኖች በሙሉ ሲከፈሉ ውሳኔው ተፈጻሚ እንደሚሆን በግልጽ መወሰን ያስፈልጋል (አንቀጽ 445)፤
- የካፒታል ዕድገት የሚፈጸምበትን መንገድ መወሰን ያስፈልጋል (አንቀጽ 442/2/)፤
- ነባር ባለአክሲዮኖች አዳዲስ የሚወጡ አክሲዮኖችን የመግዛት የቅድሚያ መብት (አንቀጽ 448)፣ያልተገዙ አክሲዮኖችን የመግዛት መብት (አንቀጽ 449) እንዲሁም ቀሪዎችን አክሲዮኖች ስለማከፋፈል (አንቀጽ 450) ወይም ነባር ባለአክሲዮኖች አዳዲስ ከሚወጡ አክሲዮኖች የመግዛት የቅድሚያ መብት በሙሉ ወይም በከፊል ተፈጻሚ እንዳይሆን ከተወሰነ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 451 የተቀመጡ ሁሉም ቅድመ ሁኔታዎችን ተከትሎ የካፒታል ዕድገት ውሳኔውን መወሰን እና መፈጸም ያስፈልጋል፡፡
- በካፒታል ዕደገት አወሳሰን ሂደት የተፈቀደ ካፒታል የሚል አገላለጽ በፍፁም ሕጋዊ መሠረት የሌለው መሆኑ ታውቆ የአክሲዮን ማህበሩ ካፒታል የተፈረመ እና የተከፈለ ከሚለው አገላለጽ ውጪ ውሳኔ ከተሰጠ ውድቅ የሚደረግ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

**ሐ. የማህበሩን ዜግነት የመለወጥ፤**

**መ. ማህበሩ እንዲፈርስ፣ ወደ ሌላ ዓይነት የንግድ ማህበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም እንዲዋሀድ የመወሰን፤**

**ሠ. ሌሎች በንግድ ሕግ** [ለምሳሌ የንግድ ሕግ አንቀጽ 268(2)፣272(3)፣275(1ሀ፣3 እና 4)፣276(1 እና2)፣278(3)፣315(6ሠ)፣452(1)፣461(1)፣462፣466፣473(3)፣475(1 እና 3)..... ይመልከቱ] **ወይም በአክሲዮን ማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ በዚህ ጉባዔ እንዲታዩ ተለይተው የተሰጡትን ጉዳዮችን የመወሰን ያካትታል፡፡**

**________________________ኢ.ብባ/ሕአዳ________________________**

## አባሪ-1

## የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ ናሙና

## ________________________አክሲዮን ማህበር

## የባለአክሲዮኖች______ኛ______ጠቅላላ ጉባዔ የጉባዔ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(___) ፣367 (___)፣ አንቀጽ____እና 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ________መሠረት የ____________________አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች______ኛ *(ስንተኛ ጉባዔ እንደሆነ ይገለጽ)* ________________ *(ዓመታዊ/ዓመታዊ ያልሆነ መደበኛ/አስቸኳይ ተብሎ ይገለጽ)* ጠቅላላ ጉባዔ__________________ቀን 201______ ከ______ ሰዓት ጀምሮ በ____________________ *(ጉባዔው የሚካሄድበት ቦታ እና አድራሻ በዝርዝር ይገለጽ)* ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባዔው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የ________________________ *(ጉባዔው የሚጠራው አካል በግልጽ ይጠቀስ)* ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

### 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

1.1 የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥርያ ቤት አድራሻ፡- *(ድረ-ገጽን ያካተተ መሆን አለበት)*

1.2 የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡-______________________________

1.3 የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ(ካፒታል)፡-__________________________

1.4 የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ(ካፒታል)፡-____________________________

### 2. የ______________________ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች[24]

2.1 ……………

2.2 ……………

2.3 ……………

### 3. ማሳሰቢያ

[24] የጉባዔው ጥሪ የተደረገው መደበኛ እና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በተከታታይ ለማካሄድ ከሆነ የእያንዳንዱ ጉባዔ አጀንዳዎች ለየብቻቸው በርዕስ ተለያይተው በማስታወቂያው በግልጽ መነገር አለባቸው፡፡ በተጨማሪ በዚህ የአጀንዳዎች ዝርዝር ስር የጉባዔው ድምጽ ቆጣሪዎችን መሰየም፣ የጉባዔውን ጸሐፊ መመረጥ ወይም መሰየም፣ የጉባዔውን አጀንዳዎች እና የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔው ማጽደቅ ወዘተ…የሚሉ ጉዳዮች የሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች እንደመሆናቸው መጠን በቃለ-ጉባዔው የግድ መካተት ያለባቸው ቢሆኑም ውሳኔ እንደሚያስፈልጋቸው መሠረታዊ የአንድ ጉባዔ አጀንዳዎች ግን በጉባዔው የጥሪ ማስታወቂያ መገለጽ/መነገር የለባቸውም፡፡ ሆኖም ይህንኑ ሀሳብ ባለመቀበል በአጀንዳዎች መልክ ከተያዙ በጉባዔው ቀን ልክ እንደሌሎች አጀንዳዎች በቅደም ተከተላቸው ዝርዝር ውይይት ተደርጎባቸው ውሳኔ የሚሰጥባቸው ስለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

3.1 በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒን በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባዔው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በ____________________ *(ቅጹ የሚሞላበት ቦታ አድራሻ ይጻፍ)* በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባዔው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡ ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

3.2 የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን ወይም ማንነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ እና እንደአስፈላጊነቱ የዲጂታል መታወቂያ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ(ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡[25]

**የ______________________አክሲዮን ማህበር_______________** *(ጥሪ ያደረገው አካል ስም ይጻፍ)፡፡*

የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ናሙና

[25] ይህ መስፈርት የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ኢ.ማ፣ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ኢ.ማ እና የባንክ ኢ.ማ ባለአክሲዮኖችን በአስገዳጅነት የሚጠየቅ ላይሆን ይችላል፡፡